# **ቁልፍ መለኪያዎች እና የማብራርያ መግለጫዎች**

*ስኬታማ የሆኑ መጪ ግዜያትን ለመገንባት በምንሰራበት ጊዜ…እያንዳንዱ ተማሪ…በየቀኑ…**Park Hill School District** (የፓርክ ሂል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት) የሚከተሉትን ተግባራት ለማከናወን ቁርጠኛ ነው፥*

## **ደህንነታቸው የተጠበቀ እና እንግዳ ተቀባይ የሆኑ ቦታዎችን መፍጠር**

*እንግዳ ተቀባይ የሆኑ ቦታዎችን በማስፋፋት እና በተግባራቶቻችን ሁሉ አካታችነትን በማከል፣ ሁሉም ሰዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ክብር እንደተሰጣቸው ሆኖ እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ቦታዎችን እንፈጥራለን።*

## **ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶችን ማሳደግ**

*ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በ DEIB ስራ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በማድረግ በኩል እምነትን እና የማህበረሰብ ተሳትፎን በማሳደግ ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶችን ለማሳደግ በቁርጠኝነት እንሰራለን።*

## **ተጠያቂነትን እንደሚኖር ግምት ውስጥ ማስገባት**

*ጉዳትን/ጥፋትን መጠገን፣ ምቾት በማይሰጡ ንግግሮች ውስጥ ተሳታፊ መሆን እና ከስህተቶቻችን መማርን እና ስህተቶቻችንን ማረም በሚሉ የማስተካከያ ልምምዶች እና ሃሳቦች አማካኝነት የተጠያቂነት ባህልን እንፈጥራለን።*

## **አካታች የሆነ ውክልና እንዲኖር ማድረግ**

*ባለን የ ሰራተኛ ሃይል፣ የትምህርት ስርዓት እና በፕሮግራሞቻችን ውስጥ አካታች የሆነ ውክልና እንዲኖር እናደርጋለን በዚህም ስራዎቻችን የምናገለግለውን ማህበረሰብ እንዲመስሉ እናደርጋለን።*

## **ዓላማ ባላው የመማር ሂደት እና በ ንግግር ውስጥ ተሳታፊ መሆን**

*ይበልት አካታች የሆነ የፓርክ ሂል ማህበረሰብን ለመገንባት በምንሰራበት ግዜ ዓላማ ባላው የመማር ሂደት እና በ ንግግር ውስጥ ተሳታፊ በመሆን፣ ዕድገታችን በመለካት እና እርስ በእርሳችን እንረዳዳለን።*

## **ታሪኮቻችንን ማጋራት እና በንግግሮቻችን ውስጥ ግልጽ መሆን**

*ከ ፓርክ ሂል ማህበረሰብ ለምንሰማቸውን ታሪኮች ክብር የምንሰጥ ሲሆን፣ እኛ ያስመዘገብናቸውን ድሎች እና የፈጠርናቸው የመማር ዕድሎችን የተመለከተ ግልጽ መልዕክት በማስተላለፍ ለ DEIB ልምምዶች/ስራዎች ያለንን ቁርጠኝነት እናሳድጋለን።*

# የገላጭ ሃረጋት ፍቺ

## *(ከ ፓርክ ሂል ቁልፍ መለኪያዎች እና የማብራርያ መግለጫዎች ጋር በተያያዘ)*

**<u>ሁሉም ሰዎች</u>**-ይህ ሁሉንም የብዝሃነት ደረጃዎች ያካትታል፡ ዕድሜ፣ ብሄር፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ ቋንቋ፣ አካላዊ እና የግንዛቤ ችሎታ፣ ዘር፣ ሃይማኖታዊ እምነቶች፣ ጾታዊ ዝንባሌ እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን

**<u>DEIB</u>**- ብዝሃነት፣ ፍትሃዊነት፣ አካታችነት እና ተቀባይነት ማግኘት

- **<u>ብዝሃነት</u>**-ከተለያዩ ውክልናዎች የመጡ ሰዎችን የማካተት ወይም የማሳተፍ ልምድ ወይም ብቃት፡-፡ ዕድሜ፣ ብሄር፣ ጾታ፣ የፆታ ማንነት፣ ቋንቋ፣ አካላዊ እና የግንዛቤ ችሎታ፣ ዘር፣ ሃይማኖታዊ እምነቶች፣ ጾታዊ ዝንባሌ እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች
- **<u>ፍትሃዊነት</u>**- ሰዎች ፍላጎታቸው ላይ በመመስረት እድሎችን የማቅረብ፣ እንቅፋቶችን የማስወገድ እና ተደራሽነት እንዲኖር የማድረግ ልምድ።
- **<u>አካታችነት</u>**- አድልዎ ሊፈጸምባቸው ወይም ሊገለሉ ለሚችሉ ሰዎች ሆን ብሎ ዕድሎችን እና አጋዥ ግብአቶችን በእኩልነት እንዲያገኙ የማድረግ ድርጊት።
- **<u>ተቀባይነት ማግኘት</u>**- ከፈተኛ እምነት/ ዝቅተኛ ጭንቀት ያለባቸው አከባቢዎችን በመፍጠር ውስጥ የሚኖር የደህንነት ስሜት፣ የመሸማቀቅ፣ ተቀባይነት ያለ ማግኘት ወይም የመጎዳት ስጋት ሳይኖር ትክክለኛ ማንነትን ማሳየት።

**<u>የማካተት ሂደት/አካታችነት</u>**- አድልዎ ሊፈጸምባቸው ወይም ሊገለሉ ለሚችሉ ሰዎች ሆን ብሎ ዕድሎችን እና አጋዥ ግብአቶችን በእኩልነት እንዲያገኙ የማድረግ ፖሊሲ ወይም ድርጊት።

**<u>የመማር ዕድሎች</u>**- የማደግ እና የመፈተን ዕድሎች ያሉበት ቦታ፣ ግለሰቦች አዳዲስ ክህሎቶችን፣ ዕውቀትን እና/ወይም ልምምዶችን እንዲያገኙ የሚያስችል አከባቢ።

**<u>የፓርክ ሂል ማህበረሰብ</u>**- በፓርክ ሂል ትምህርት ቤት ዲስትሪክት ውስጥ የሚያገለግሉት ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ የማህበረሰብ አባላት እና አገልግሎት አቅራቢዎች።

**<u>ዓላማ ያለው የመማር ሂደት</u>**- ያሉብን የ DEIB ቃልኪዳኖችን እና ልምምዶችን የሚደግፉ የትምህርት ርእሶች እና ጽንሰ ሃሳቦች ላይ ትኩረቱን ያደረገ ትምህርት።

**<u>የማሰተካከያ ስራዎች</u>**- በግለሰቦች መካከል እንደዚሁም በማህበረሰብ ውስጥ የሚኖርን ማህበራዊ ግንኙነት እንዴት ማጠናከር እንደሚቻል የሚያጠና ማህበራዊ ሳይንስ ነው፡ ሰዎች ተገቢ ያልሆኑ ባህሪያትን በሚያሳዩበት ግዜ፣ ነገሮችን ለማስተካከል ሊበረታቱ ይገባል፣ ይህም የድርጊቶቻቸውን ተፈጥሮአዊ መዘዞች እንዲጋፈጡ ማድረግን ሊያካትት ይችላል።

**<u>ባለድርሻ አካላት</u>**- ሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ የማህበረሰብ አባላት እና የአገልግሎት አቅራቢዎች።

**<u>ምቾትን የማይሰጡ ንግግሮች</u>**- ስለ ተለያዩ አመለካከቶች እና አስተሳሰቦች የበለጠ እንድንማር የሚጋብዙን ንግግሮች;ነገሮችን ይበልጥ አስፍተን እንድናይ እናም በዚህም እንድናድግ እና እንድንማር የሚያደርጉን ንግግሮች።